# የየካቲት 12 የሰማዕታት ቀን መታሰቢያ በሮም



በኢጣሊያን በሮማ ከተማ የካቲት 12 የሰማዕታት ቀን በሚመለከት ቅዳሜ የካቲት 14-2007 የተሳካ ስብሰባ ተካሄደ። ስብሰባውን የከፈቱት አቶ ካርሜሎ ክርሽንቲ (ገብረ ሥላሴ ደስታ) ስለተደረገው ጭፍጨፋ በሰፊው አስረድተዋል። ከዛም ወሮ አስካለ ክፍሉን ወደ መድረኩ ጋብዘዋል።



ወይዘሮ አስካለ ምንም እንኳን ከጦርነቱ በኋላ ቢወለዱም በሕጻንነታቸው የሰሙትን ለተሰብሳቢዎች በማስረዳት የደረሰውን ጭፍጨፋ አስረድተዋል። በተለይም በቅርብ ዘመዶቻቸው ላይ የተፈጸመውን ግፍ በሚያሳዝን ቃላት አስረድተዋል። አቶ ፍራንቸስኮ ቫሎሬ በማስተርጎም ተባብረዋል።



ከዛም የሮም ከተማ ፈሽዝምን የተዋጉ አርበኞች ማሕበር ሊቀመንበር አቶ እርኔስቶ ናሲ በሰፊው በጣሊያን ስለተደረገው ትግል ካስረዱ በኋላ በተለይም በአፊሌ ከተማ እየተሰራ ያለውን የግራዚያኒ ሃውልት በሚመለከት በሚቀጥለው መስከረም ወር ላይ ፍርድ ቤት እንደተቀጠረ አስታውቀዋል።



በመቀጠልም ወይዘሮ ሙሉ አየለ በጦርነቱ ወቅት የሴቶችን ተሳትፎ በሚመለከት ሰፋ ያለ ዘገባ አቅርበዋል። በተለይ በአሁኑ ወቅት የግራዚያኒን ሃውልት በሚመለከት ሁላችንም ጎን ለጎን ሆነን መታገል እንዳለብን አሳስበዋል።



አቶ በላይ ምስግና በጦርነቱ ውስጥ የሞት ቅጣት የተፈጸመባቸውን ጀግኖችን በሚመለከት ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተዋል። በተለይ ስለ ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ የሕይወት ታሪክ ለተሰብሳቢው አስረድተዋል።



በመጨረሻም የግራዚያኒ ሃውልት በተሰራበት ከተማ የተቋቋመው ኮሚቴ ቃል አቀባይ የሆነው ወጣት ማቴው አሁንም የግራዚያኒን ሃውልት ለማስፈረስ የሚደረገው ትግል እንደሚቀጥል አስታውቆ በተለይ ዛሬ በዚህ ስብሰባ ያየኋቸው መረጃዎች ሁሉ የተሰራውን ግፍ የሚስታውሱን ይሆናሉ። ስለዚህም ትግላችን መቀጠል ይኖርብናል በማለት አሳስቧል።